# SEE - Clean Cooking

## Higher Tier Cooking Component – Ethiopia

## Result Based Financing - Call for application - ማስታወቂያ

SEE – Clean Cooking

Co-financed by: Ministry of Foreign Affairs; Ministry of Foreign Affairs of Denmark DANIDA International Development Cooperation
Coordinated by: Netherlands Enterprise Agency
In partnership with: endev
Implemented by giz Deutsche Gesellschaft für Internationale Zusammenarbeit (GIZ) GmbH; SNV

## ማስታወቂያ

ኤስ ኤን ቪ በእስያ፣ አፍሪካና ላቲን አሜሪካ በሚገኙ 28 በሚሆኑ ታዳጊ ሀገሮች ሀገር በቀል በሆኑ የማህበረሰቡ ተቋማትና ድርጅቶች በኩል ገበያን መሠረት ያደረገ መፍትሄዎችን ለማህበረሰቡ የሚሰጥና የሚሰራ ድርጅት ነዉ። http://www.snv.org

ኤስ ኤን ቪ በግብርና፣ ኢነርጂ እና ዉሃ፣ ንፅህና እና ጤና አጠባበቅ ዘርፍ በመሥራት የረጅም ጊዜ ልምድ ያለዉና እየሰራ ያለ ድርጅት ነዉ። የድርጅቱ የአለም አቀፍና የሃገር ዉስጥ ከፍተኛ ባለሙያዎች ከአጋር አካላት ጋር በመሆን ማህበረሰቡ፣ የንግድ ተቋማቶችና ድርጅቶች መሰረታዊ የሆኑ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ፣ ገቢያቸዉን እንዲያሳድጉ፣ ከድህነት እንዲወጡ እና የራሳቸዉን እድገት በራሳቸዉ እንዲመሩና ብቁ እንዲሆኑ የሚያስፈልጋቸዉን ግብዓቶች እንዲያገኙ፣ እዉቀትና ክህሎት እንዲኖራቸዉ እና የስራ ትስስር እንዲፈጥሩ ይሰራል።

ኤስ ኤን ቪ ከፍተኛ የጥራት ደረጃ ያላቸዉ 20,000(75% የኤሌክትሪክና 25% በማገዶ የሚሰሩ) ምድጃዎችን ገዝተዉ ለሚጠቀሙ ተጠቃሚዎች የሚሸጡ በዘርፉ የተሰማሩ፣ ብቁና ፈቃደኛ የሆኑ አገለግሎት ሰጭ ድርጅቶችን/ ነጋዴዎችን በጨሬታ ማሳተፍ ይፈልጋል። የሚመረጡት አገለግሎት ሰጭ ድርጅቶች ቁጥር 10 ይሆናሉ። ይህን የምድጃ ግብይት እንዲሰሩ ለተመረጡ ድርጅቶች የስራ ዉጤትንና አፈፃፀምን መሰረት ያደረገ የገንዘብ ማበረታቻ/**RBF** የሚሰጥ ሲሆን ክፍያዉ በምድጃ አይነትና ብዛት በዉል ወቅት ቅድመ ክፍያና ቀሪዉ ምድጃዎቹ ከተሸጡ በኋላ የሚከፈል ሲሆን ይህ ማበረታቻ አስፈላጊነቱ የምድጃ ገበያን ለማነቃቃትና ተደራሽነትን ለማስፋፋት ነዉ።

**አገልግሎት ለመስጠት ብቁ የሚሆኑ ድርጅቶች ማሟላት ያለባቸዉ መሰፈርቶች**

አፈፃፀምን መሰረት አድርጎ የሚሰጠዉን የገንዘብ ማበረታቻ ለማግኘት የሚፈልግ ድርጅት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት።

- በሚመለከተዉ የኢትዮጵያ ህግ መሰረት የተመዘገበና ፈቃድ ያለዉ/ያላት
- በምግብ ማብሰያ ምድጃዎች አስመጪነት፣ አምራችነት፣ አከፋፋይነት፣ ሻጭነት፣ የሽያጭ ወኪልነት ስራ የተሰማራና እየሰራ ያለ/ች
- ከፍተኛ ደረጃ ጥራትና ብቃት ያላችዉ የምግብ ማብሰያና መጋገሪያ ምድጃዎችን ለተጠቃሚዎች እየሸጡ ያሉ
- ሴት አመልካቾች ይበረታታሉ። ይህም ሲባል የድርጅቱ ባለቤት ሴት የሆነች፣ በሴት ስራ አስኪጅ የሚተዳደርና ብዛት ያላቸዉ ሴቶችን ቀጥሮ የሚሰራ ድርጅትን ያካትታል።

**ለግብይት የሚዉሉ ምድጃዎች የጥራት መስፈርት**

አፈፃፀምን መሰረት አድርጎ በሚሰጠዉ የገንዘብ ማበረታቻ ስርዓት ለተጠቃሚዎች የሚሸጡት የምግብ ማብሰያ ምድጃዎች ብቁ እንደሆኑ ማሟላት የሚገባቸዉን መስፈርቶች ማሟላት ያለባቸዉ ሲሆን እነሱም የሚከተሉት ሆነዉ በእነዚህ ብቻ ግን የተገደበ አይደለም።

- **የጥራት ደረጃ፡** ደረጃ ሶስትና ከዚያ በላይ። ይህም ዉጤታማነትን፣ ብቃትንና አፈጻፀምን ያካትታል
- **ጠቀሜታ**፡ ለምግብ ማብሰያና መጋገሪያ አገልግሎት የሚሰጡ
- **የነዳጅ/የሀይል አይነት፡** በኤሌክትሪክ እና በባዮማስ/ማገዶ እንጨት የሚሰሩ። የኤልፒጂ/ቡታጋዝ ምድጃዎችን አያካትትም
- **የምድጃዎች ስሪት/ምንጭ፡** ሀገር ዉሥጥ የሚመረቱና ከሀገር ዉጭ ተመርተዉ ወደ ሀገር የሚገቡ
- **ተጨማሪ አገልግሎት፡** ከሽያጭ በኋላ የጥገና አገለግሎት እና የጊዜ ገደብ ያለዉ ዋስትና መስጠት የሚችል
- **የምድጃ አይነት፡** የኤሌክትሪክ ምድጃዎች( የእንጀራ መጋገሪያ፣ የምገብ ማብሰያ፣ የፕሬዠር ኩከር፣ የዉሃ ማሞቂያ፣ የኢንፍራሬድ ማብሰያ፣ኢንዳክሽን ማብሰያ፣ ጋዝፋየር ማብሰያና የመሳሰሉት)፣ በኢታኖል የሚሰራ ማብሰያ እና በከፍተኛ ደረጃ የተሻሻሉ በማገዶ/ባዮማስ የሚሰሩ ምድጃዎች።

**አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች የሚመረጡበት መስፈርት**

አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶችን ለመምረጥ ሁለት የመረጣ ደረጃዎች የሚኖሩ ሲሆን ይህም ድርጅቶቹ በሚያቀርቡት የቴክኒካል እና የፋይናንሻል ፕሮፖዛል መሠረት ይሆናል። ቴክኒካል ፕሮፖዛሉ አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች በምን አይነት መንገድ ግብይቱን እንደሚሰሩትና ምድጃዎችን ለመሸጥ እንደሚችሉ እና የሚያጋጥሙ የግብይት ተግዳሮቶችን በመቅረፍ ለተጠቃሚዎች ማድረስ እንደሚችሉ በግልፅ ማሳየት አለበት። የፋይናንሻል ፕሮፖዛሉ አገልግሎት ሰጭ ድርጅቱ ለግብይት የሚያዉላቸዉን ምድጃዎች በምን ያህል ወጋ ለተጠቃሚዎች እንደሚሸጥና እነዚህን ምድጃዎች በተጠቀሰዉ ዋጋ ለመሸጥ በእያንዳንዱ ምድጃ ምን ያህል የማበረታቻ ገንዘብ እንደሚፈልግ በገልፅ ማሳየት አለበት። ምርጫዉም አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶቹ በሚያቀርቡት ዝቅተኛ የምድጃ የመሸጫ ዋጋ እና በተጠየቀዉ ዝቅተኛ የማበረታቻ የገንዘብ መጠን ይከናወናል።

የመንገድ ተደራሽነት አነስተኛ በሆነባቸዉና ሩቅ የሆኑ አካባቢዎችን አገልግሎት ለመስጠት ፈቃደኛ ለሆኑ እና ምደጃዎችን በቀላሉ ለማያገኙ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላላቸዉ የማህበረሰብ ክፍሎች (የገቢ መጠናቸዉ አነሰተኛ የሆኑ፣ እማዎራዎችንና አቅመ ደካማዎችን) አገልግሎት ለሚሰጡ ድርጅቶች የተሻለ ማበረታቻ ይደረጋል።

ይህ የአገልግሎት ጨሬታ የሚቆየዉ እስከ ህዳር 04/2016 ዓ.ም ብቻ ሲሆን ከታች በተቀመጠዉ አድራሻ ወይም Ethiojobs.net አማካኝነት የጨሬታዉን ሙሉ መረጃ በማየት በአካል ወይም በኢሚል ettenders@snv.org ማካኝነት ማመልከት ይቻላል።

**ማሳሰቢያ**

- ከተጠቀሰዉ ቀን ዘግይቶ የሚመጣ ሰነድ ተቀባይነት የለዉም
- በጨሬታዉ መሳተፍ የሚፈለግና መስፈርቱን የሚያሟላ ማንኛዉም አካል ሙሉ የጨሬታዉን መረጃና የማመልከቻ ፎርም አዲስ አበባ፣ ሀዋሳ፣ አዳማ፣ መቀሌ፣ባህርዳር እና ድሬደዋ በሚገኙት የኤስ ኤን ቪ ቢሮዎች, Ethiojobs.net ወይም ከታች በተገለፀዉ የድርጅቱ አድራሻ ማግኘት ይችላል።
- ፕሮፖዛሉ የተፈረመበትና የድርጅቱ ማህተም የተደረገበት መሆን አለበት
- ለግብይት የሚዉሉትና በፕሮፖዛሉ የሚካተቱት ምድጃዎች ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸዉ
- አመልካቾች የታደሰ የንግድ ፈቃድና ሌሎች ህጋዊ መረጃዎችን እና በኤስ ኤን ቪ ፎርም መሰረት የተሞላ የፍይናንሻል ፕሮፖዛል አሟልተዉ ማቅረብ አለባቸዉ
- ኤስ ኤን ቪ ኢትዮጵያ ጨሬታዉን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰዝ መብቱ የተጠበቀ ነዉ።
- ስለፎርሙ አሞላል እና ስለ RBF ገለጻ ጥቅምት 22/2016 ዓ.ም ኤስ ኤን ቪ ዋናዉ ቢሮ ከጧት 4፡00 እና በኦን ላይን (Click here to join the meeting) ጥቅምት 23/2023ዓ.ም ከ4፡00- 6፡00 ይሰጣል።

**አድራሻ**

ኤስ ኤን ቪ ኢትዮጵያ ዋና ቢሮ: ሎጅስቲክ ዲፓርትመንት፣ ከአፍሪካ አንድነት ድርጅት ወደ ሜክሲኮ አደባባይ በሚወስደዉ መንገድ ሸበሌ ክሊኒክ አጠገብ, ፖ.ቁ 40675, ስ.ቁ +251 116 166232/238፣ ፋክስ ቁጥር +251-116166252 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ.